# የትግል ብኸርታ

የሚሄድብትን መንገድ የማያውቅ ጉዞኛ፡ ወይም ገድል አፋፍ ጫፍ ይደርሳል ወይም ጅንጀሮ የማይወጣው የዐለት ተራራ ስር ሲደርስ፡ ቀና ቢል ሰማይ ጎንበስ ቢል ምድር፡ ከማየት በስተቀር አንድ እርምጃ እንኳን ወደፊት ለመሄድ ቢሞክር ወይም ገደሉ ዉስጥ ገብቶ የአዉሬ እራት ይሆናል፡ አልያም ከዐለቱ ጋር ተጋጭቶ የእንግላሊት ወድቆ ሳሪሳራው ተበጥሶ ለዘላለሙ ያልጋ ቁራኛ ሆኖ ይቀራል። አዎ የኛ የሰላም ታጋዮችም ሳሪሳራቸው ተመቶ ፓርላማ ይተኛሉ።

ጉዞ ሲጀመር መድረሻን አውቆ ስንቅን ሰንቆ የት እንድሚዋል የት እንደሚታደር፡ ጉዞው ምን ያክል አድካሚና ስንት ዉጣ ውረድ እንዳለው ተረድቶ፡ ለአቀበቱ የማይለግም ለቁልቁለቱም የማይብረከረክ ጉልበት፡ በጽሀይ ሀሩሩ የማይጠወልግ ገጽታ፡ በዶፍ ዝናብ በውሃ ፈረሰኛ ይማይብረግግ ልብ፡ ሃሞተ ኮስታራ ልበ ደንዳናነትንና ቆራትነትን ይጠይቃል።

ይህ አይነት የስነልቦና ዝግጅት የሌለው፡ ጉማሬ ለማደን ገና ከቤቱ ሳይወጣ ከቅየው ሳይርቅ ዎፍ በጮኸ ቁጥር የግራ ዋሳ ጮኸ ወይ ጉዴ -የቀኝ ዋሳ ገመዴ እያለ ከበሩ ለመውጣት ሲአመነታ የልቡ ትርታ ቻቻ ሲመታ ፡ ቀልቡ ሲገፈፍ፡ አጋ ምሽት ጅብ በጮኸ ቁጥር ሰዉነቱ እንደ ጭዳ ሲቀደድ፡ አይ ጸጸቴን እያፏጨ ምስጥ ፍልፈላ የገነባውን ኩይሳው በሰው ተመስሎ ከፊቱ ተበግሮ በላሁህ እያለ ሲያስፈራራው፡ በቀኝ እጁ አማልክትን በግራው ደሞ የአሩሲዋን እመቤት የጎጃሙን ቡሬ መጀን በናንተ ዉቃቤ ሲል፡ በቀዝቃዛው ምሽት በራሱ ላቦት ተዘፍቆ ዶፍ ዝናብ የወረደበት ይመስል መጠጊያ ታዛ ሲፈልግ፡ ክብርት ባለቤቱ የሰነቀችለትን ዳቦቆሎ ለበርሃ አይጠሞገጥ አስረክቦ ለጉማሬ ማደኛ የተሸከመውን ነፍጥ ለአይጠሞገጥ መከላከያ እንኳን ሳያደርገው እንደ እማሆይ ምርኩዝ በይአረንቁዋው ሲዘፍቀው፣ እራሱን በራሱ እየሞገተ ወይኔ ወንዱ እያለ ፍርሃቱን በፉጨት ሲሸፍን፡ የፈሰሰ ሃሞቱን የሸና ወኔውን እስትንፋሱ ውጦት፡ አንድም ወደፊት አይሄድ ወይ ወደ ኋላ አይመለስ መንታ መንገድ ላይ ቁሞ ሲያምነታ፡ ድንገት የባለቤቱ ዛላ ትዉስ ብሎት፣ ምንአባቱንስና ብሎ እንባዉን ዝርግፍ ዝርግፍ አርጎ ያ ቁንዳላሽ ገና ካሁኑ እንዲህ የናፈቀኝ ሁለት ወር ስቆይማ አንጎል መሆኔ አይቀርም በሚል እራሱን አጽናንቶ መጀመሪያ ቀን በአጋጣሚ የገደለውን ጅንጀሮ ይሁን የአሽኮኮ ጸጉር ባራሱ ላይ ቆልሎ፡ ጉዞው ቀቢጸ ተስፋ የለሽ መሆኑን ተረድቶ አሁን ያደንኩት ጅንጀሮ ለኋለኛው ጉማሬ ግድያ መንገድ ይከፍታል። "ሰናይ ውእቱ" ድንቅ ነው መልካም እድል ነው፣ እንዲያውም ይህ ጥሩ መላ ነው፡ በአንድ ጊዜ ብዙ መመኘት አይበጅም ብሎ ጉማሬ ሊያድን ጉዞ ከጀመረበት ቀየው በጎበዞች መሃል በሚስቱ ፊት ቁሞ፤

"ዘራፍ ያንቺ አሽከር ያንቺ ቅምጥል
ሳይዝ አይገባ ሳያነጠለጥል
ዘራፍ እትትት....

ያለው ሰውዬ፣ ለረጅም ግዜ ታስቦ ተሰንቆ የተሸኘው አዳኝ፣ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ዘራፍ ወደአለባት በራፉ ሳይታሰብ ከተፍ ሲል አቶ ባል አዳኙ መጡ ተባለና ወይዘሮ ሚስቲቱ እልልታውን ስታቀልጠው ጎበዞች ጉማሬ አዳኙ ጉማሬ ያጋደመ መስሏቸው ተሯሩጠው ሲገቡ የጎበዝ አለቃው ያሽኮኮውን ጸጉረ አየት አርጎ 'ጀግናው ወንድማችን ጉማሬ ሊአድን ሄዶ ጉማሬ ሁኖ መጣ፡ አለና ሲዛብትበት የስሙት አዛውንት ጉማሬ መሆኑ አይግረምህ የጉማሬውን ቆዳ የምታጸዳውን ወፍ እንዳይሆን ፍራልኝ አሉና... በአዳኙ ዉሸት ተጸይፈው ድሮስ ቢሆን የሌለበትን ወኔ አለው ብላችሁ እንጅ አዳኝ አገር ጫቆ ጎበዝ የጠፋ ይመስል የዚያ ጀግና ልጅ "ያባቱ አጥንት እሾህ ሁኖ ይውጋው" እንጂ እንደ ጉማሬ ባፉ በልቶ ባፉ ...እንትን የሚል.. በስመ አብ በስመ

ወልድ ብለው ሳይጨርሱ ምን ያለው ዘመን መጣብን እያሉ እጃቸውን እያወራጩ  አየ አንተ ጌታ የለህማ! ብለው... አቅም ተስኗቸው ወገባቸውን ባአንድ እጃቸው ደገፍ አርገው ራቅ ብሎ ካለው ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው በያዙት በትር መሬቱን መቆርቆር ጀመሩ... እዉነት ነው የጉማሬው መለስ ዜናዊ ለቃሚ ወፍ ይሆናሉ።

አዎ ሁላችንም መሬት እየቆረቆርን ክንፈር እየነከስን በየፊናችን ተቀምጠን ይሆናል፣ አዎ ለኢትዮጵያችን ሲሉ ለህዝብና ሀገራዊ አንድንት፡ ለዴሞክራሲ፡ ለነጻነት፡ለፍትህና ርትዕ፡ ሲሉ ማንም ሳይጠይቃቸውና ሳያስገድዳቸው ከህዝባቸው ፍቅር የመነጨ በወዶ-ገባነት የህዝብ ወታደር ሆነው መተኪያ የሌለዉን ክቡር ህይወታቸውን በደስታ ከፍለው አልፈዋል።

ትግላችን የሚኝዝበትን መንገድ ስቶ አውላላ ባህር ዉስጥ ገብቶ ሲዋዥቅ አቅጣጫ የሚሰጠውና ወደ  እውነተኛ ኤትዮጵያዊነት የትግል መስመር የሚመራው አጥቶ ባለበት ባሁኑ ስዐት ሁላችንም በአንድ ድምጽ የመሪ ያለህ ብለን መጮህ ግዴታችን ነው።

የመሪ እጦቱ ጉዳይ ከምጊዜውም በበለጠ ዛሬ አይኑን አፍጥቶ ጥርሱን አግጥጦ የተከሰተበት ወቅት በመሆኑ ማንኛዉም በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ያለ ሁሉ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በሚደረግ ማንኛዉም አይነት ስምምነት፡- የፖለቲካ ይሁን የኤኮኖሚ ድርድሮች፡ የአንድን ኢትዮጵያዊ ህይወት በክፉም ይሁን በደግ የሚነኩ ስምምነቶች በቀጥታ ስለሚመለከቱን ደጉን ደግ ብለን ማዎደስ ግሙንና ክፉዉን ደግሞ መንቀፍ መምከር ከዚያም አልፎ ቢቻል መክሰስ አለያም እስከ ማውገዝ ድረስ መሄድ ትግሉና የተበደለው የተከፋው ድምጽ የለሹ ህዝባችን ከኛ የሚጠብቅብን ግዴታ ነው። ይሄን ግዴታና ሀላፊነት ለአንድ አፍታ እንኳን ልንዘነጋው አንችልም። ምክኒያቱም በህዝብ ትግል መሪ ስም እራሳቸዉን የሾሙ የፖለቲካ ገቢያ ቸርቻሪዎችና አትራፊዎች (POLITICAL RETAILERS AND PROFITAIRS) በዉስጣችን ነበሩ አሁንም አሉ ወደፊትም ይኖራሉ። ይህ ደግሞ እድል ሆኖ ለኛ ብቻ የተሰጠ እርግማን ሳይሆን በማንኛዉም ሃገር በተለያየ የፖለቲካ እና የኤኮኖሚ ቀዉስ በሚፈጠርበት ወቅት የሚከሰት ክስተት ነው፡፡ የህብረተሰብ ኗሪ ጉድፍ ነውና።

ከዚህም ጋር ተያይዞ የኛም ሀላፊነት በእንደዚህ ያለ ጊዜ የበለጠ ፊት ለፊት መጋፈጥን፡ አለማወላዎልን፡ ይሉንታን ያላካተተ፡ የጠራና የሰላ ኢትዮጵያዊንትን የሚአስከብር ትግል መታገል ይጠበቅብናል።

አመድ ላይ ተወዝፎ የሚውል እግር የሙጀሌ ማህደር ከመሆኑም ሌላ እምቧይ ሲለቀለቅ ይኖርና የመጨረሻ ዕድሉ ሽፋፋ ሆኖ ባለቤቱም እንትና ሽፎ እንደተባል ይሞታል፡ የኛም የፖለቲካ መሪዎች ድርጅታቸውን ሲፈጥሩ ቀጥ ያለ ያዉሮፕላን ነጅ እግር ይዘው ይመጡና እንደ ጉማሬ አዳኙ ሳምንት ሳይሞላቸው ጉሮ ወሸባዬ በሉልን ማለት የሙጅሌ ፖለቲካ ይሆናል። ለእንደዚህ አይነቱ የሙጅሌ ፖለቲካ መሪና አመራር የምንሰጠው የሰንኮፉ መንቀያ እሙቧይ ቢኖር ታጋይ ወገኖቻችንን ተወት አርጉና የህዝብን ጥያቄ ሳታውገረግሩ ስራን ለሰሪው እሾህን ላጣሪው ብላችሁ ለሚታገሉት ቅን አባሎቻችሁ አስረክባችሁ መዉጣት ይጠበቅባችኳል፡ ይህን እስከአላደረጋችሁ ድረስ ፡-

እመቤቴ ማርያም ለጌታ እየሱስ ክርስቶስ፡
"የታህሳስ ባዕታን
የግንቦት ልደታን
የየካቲት ኪዳነ ምሕረትን"

ያልተዘከረልኝ
እኔም አለምንህ አንተም አትማርልኝ፡

ብላ እንደየተማፀነችው ሁሉ እኛም ላንምራችሁ የኢትዮጵያን ህዝብም ምህረት እንዲአደርግላችሁ የማንጠይቅበት ደረጃ ላይ ተዳርሰናል፡ ለዚህም ተጠያቂዎች እናንተዉ ናችሁ። ባደባባይ ይቅርታ ጠይቆ በጓዳ ስላም የሚባባል ልደቱ ብቻ ነውና እሱም ከይቅርታ በላይ አግኝቷልና እኛም ከዚያም ነጻና ግልጽ ሆነን ከእግዲህ ጎራ ለይተናል።

አባቶቻችን ያወርሱንን ያገር ጠብቅ አደራ አረበኞች ሲወለዱ ተንከባክበን ማሳደግና ተገቢ ቦታቸውን መስጠት እንደሚጠበቅብን ሁሉ እነዚያው አባቶች አገርን ከድቶ ከጠሊያን ጋር የወገነዉን ከሃዲ ባንዳ እንዳሉት ሁሉ እኛም ካሃዲዉን ሁሉ ባንዳ እንልዋለን፡፡ ይህን ቃል የሚጠሉ ታሪካዊ አመጣጡን የማያዉቁ ናቸዉና እነ ሙንጣዝ፡ እነ ሹልቅባሽ እነ ሹምባሽ የሚባሉት ሹመቶች ሁሉ የወል ስማችው ባንዳ ነው። ይህን ታሪክ ለማታዉቁ ሁሉ ኢህአፓ ለመኤሶን የፈጠረው ስም ሳይሆን ከአበኞች አጠራር ቆንፀል አርጎ የወሰደው ነው። ስልሆነም በአሁኑ ሁኔታ አገራችን ኢትዮጵያ በስጦታና ብችርቻሮ እየተበጣጠሰች ባልችበት ወቅት እነ ኃይሉ ሻዎል የደንብር ጥያቄ ገና የሚጠና ጉዳይ ነው እያሉ በሌላ በኩል ከግራዚያኒ መለስ ጋር ህዝብን ማነቆ ዉስጥ ከተው ሲፈራረሙ ባንዳ ወዲ ሻውል አትበሉ የሚሉን የኢትዮጵያን ህዝብ ትህትና አክብሮት ዝቅ አርገው የሚያዩ ብቻ ናቸው፡፡ ህዝብ ሲበደል አገር ሲራቆት አትናገሩ አትበሉን፡ ሃሞቱ በፈሰሰ ጡንቻዉ በለሰለሰ አምሮው በደነዘዘ የአልሞት ባይ ተጋዳይ አልቃሽ ዎይዋይታና ምሾ ተባባሪና አዛኝ ሆነን ከንፈራችንን አንመጥም፡ እነዚሁ አልቃሾች ዞር ብለው እንደ ላሊበላ ማሲንቆ ይዘው የእርግማን ነተራቸውን ቢዘረግፉብን ወደኃላ አንልም። ከሀዲን ከሀዲ ለማለት ከፈራን አገር ትፈርሳለችና ልባችሁ ከባባ የትግሉን ሜዳ ለቀቅ ማረግ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በልጆቿ ትከበራለች!!

ከእያዩ ቢወጣ